# ከሃዲዎችና ባንዳዎች
# የኢትዮጵያን አኩሪ ታሪክና አንድነት
# ሊያንኳስሱትና ሊቀይሩት አይችሉም

*ከቀመሩ ደሳለኝ*

የኛ ቀደምት ትውልዶች ትውልድን ሊቀርጹና ሊያንጹ የሚችሉ ቁም ነገሮችን አውርሰው ያለፉ፣ የዜግነት ግዴታቸውን በሙሉ የተወጡ አኩሪ ታሪክ ያተረፉ እንጂ እንደነ አቶ አንዳርጋቸው (በትናቸው) ፅጌ ግንቦት 7 ጸያፍ አነጋገር አሳፋሪ ታሪክ አልተውልንም። አለኝታና መመኪያ ኢትዮጵያዊነትን አውርሰውናል። አዎ! እውነት ነው! ኢትዮጵያዊነትን ከወላጆቹም ሆነ ከኅብረተሰቡ ያልተማረ ትውልድ እንዴት ኢትዮጵያዊ ይሁን !!

ኢትዮጵያን፣ ሕዝቧንና ታሪኳን ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል። ኢትዮጵያን በጥሩ ሁኔታ ተገንዝቦና አውቆ ኢትዮጵያዊነትን የሚያስቀድም፣ በኢትዮጵያዊነቱ የሚኰራ ትውልድ መሆን በፊታችን ለተደቀነብን ችግር መፍትሔ ለማግኘት የዚህ ትውልድና የኢትዮጵያስ የወደፊት ዕጣ ምን ይሆናል ብሎ ሁላችንንም በብርቱ ሊያሳስበን የሚገባ አገራዊ ጉዳይ ነው።

እንደ ግንቦት 7 ባንዳዎች በተገኘው አጋጣሚ የሚበሉትን በልተው፣ አፋርሰውና አፍርሰው ፈትለክ የሚሉ እንጂ እንደ ኢትዮጵያ ጀግኖች አባቶቻችን ጠላትን የሚሞግቱ አይደሉምና ከነዚህ አይነቱ ድርጅቶች ጋር መተባበርና አብሮ መዋል፣ መታየት አያስፈልግም። ከሃዲ- ባንዳዎች ናቸውና።

ኢትዮጵያን ለመገነጣጠልና ለማዳከም የወያኔን የአፍራሽነት ባህሪ ተከትሎ የሚመራ፣ የሕዝቧን አንድነት ከሚጠሉ ጋር መዋልና እነሱንም በማስተባበር ተዋናኝ መሆን፣ የራሱን የተገንጣይ ባህሪ የሚያንጸባርቅ፣ የሚያሳይ ድርጅት ብቻ ነው። ለዚህም ነው ግንቦት 7 ለኦነግና ኦብነግ ዋና ሰባኪ ሆኖ የተነሳው።

ግንቦት 7 የፀረ- ኢትዮጵያና ፀረ- አንድነት አሰባሳቢ የአስገንጣይ ኃይሎች ዋና ተዋናኝነቱ የወያኔ ግልብጥ ያደፈ ሸሚዝ ለመሆኑ መሰሪ ስውር አጀንዳቸው እየተጋለጠ ነው። ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ጥንትም ወያኔ ዛሬም የተዳቀለ የወያኔ አጀንዳ እንዳለው ከጅምሩ ቢታወቅም ቅንጅትን ካፈረሰ በኋላ ለኢትዮጵያ አሳሳቢ ድርጅት እንደሆነ ራሱን ይፋ እያደረገ እንደመጣ ማንም አገር ወዳድ ኃይሎችና ግለሰብ የተረዳው ግልጽ ሃቅ ነው።

የኢትዮጵያን፣ ታላቅና ጥልቅ አገራዊነት፣ የሕዝቧን አንድነት፣ የፍቅርና ኃያልነት፣ ጥንታዊ ሥርዓት-ማኅበር፣ ያስተሳሰብ፣ ያስተያየት፣ ያሰራርና አፈጻጸምነት ልምድን ለማወቅና ለመረዳት ጥረት የማያደርግ ድርጅትም ሆነ ግለሰብ የአገርን ጉዳይ ተግባራዊ ሊያደርግ አይችልም።

ፖለቲካ በሳይንስነት አንፃር ካልታዬና ካልተቀረበ በስተቀር መፎከሪያ ብቻ ሆኖ ይቀራል። ችግርን፣ የራስን ሚና መረዳት አለመቻል፣ የማሰብ ኃይልንና እውቀትን ከታሪካዊ ግንዛቤ ጋር አጣጥሞና ተጠቅሞ በግልጽ የሚታዩ ችግሮችን ለማስወገድ አለመጣርና በራስ ክልል ብቻ እየተሽከረከሩ ማውራትና ከእውነት እየሸሹ መኖር ችግሮችን ያባብሳል፣ መፍትሔ እንዳይገኝለት እንቅፋት ይሆናል። ጠለቅ ብሎ ለአገር ወገን አንድነት ማሰብ መቻል፣ ጥናት ማድረግና መወያየት ብልህነት የተሞላበት መፍትሄ ነው።

ዴሞክራሲያዊ- ሰብዓዊ መብትን ለማስከበር፣ ለአንድ አገር፣ የአንድነት ብልጽግናንና ኃይልን በጋራ ማስተባበር እንጂ፣ መገንጠልና ትንሽ አድርጎ መሸራረፍና ማዳከም የኅብረተሰብ ትግል ሳይሆን የከፋፍለህ ግዛው የአምባገነን- ፋሽስት ሥርዓት ነው።

ግንቦት 7 የሚያደርገው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን አውግዞ ለኦነግና ኦብነግ ትብብር እንዲፈጠር መጣርና አዝማች፣ አፈ-ቀላጤ መሆን ፀረ- ኢትዮጵያ፣ ፀረ- አንድነት ባህሪን ማጠናከር ለአንድነታችን የለየለት ደመኛ መሆን ነው። ይህን መሰል እኩይ ሥራ የአንድነት ኃይሉ አጥብቆ ይቃወመዋል፣ አንድነቱንም እንደቀደምት አባቶች ያስጠብቃል።

ማወቅ ለተሳናቸው ግብዝነታቸው ለበዛ ተገንጣዮች፤ ትዕግሥታችን ፍርሃት ልመናችን ድክመት ስለመሰላቸው ፍንጠዛ አበዙብን። አቶ አንዳርጋቸው(በትናቸው) የኢትዮጵያን ታሪክ አፉን ሞልቶ <u>አሳፋሪ</u> ነው፣ <u>አንድነት</u> የሚል ቃል መጠቀም የለብንም ሲል በቃለ መጠይቅ ላይ ተደምጧል። ይህ ወያኔነትን፣ የአገር ማፍረስን አጀንዳ የሚያራምድ ለመሆኑ ግልጽ የኦነግና ኦብነግን አጀንዳንም በተመሳሳይ ለማራመድ ማቀዱን፣ ልቅ አነጋገሩንና መረን ሥራቸውን እያስተጋባ ነው።

ጥፋቷን የሚመኙ ታሪኳን ያንኳስሳሉ በአፍ ይጠፉ በለፈለፉ ነውና ዶ/ር ጌታቸው በጋሻውም ለአንደበቱ ልክ ልጓም አጣና ራሱን መግታት ተስኖት አሁንም ደጋግሞ ለእኛ መካሪና አሳቢ በመምሰል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ስለ ኦነግና አብነግ ብዙ

ለማተት እየሞከረ "አደብ ግዙ" ይለናል። ይገርማል፣ የማይሰማ የለምና !! የተማረ ከሃዲ ከመሆን አድነን ነው !! አደብ ከተነሳ እንደሱ ያለ ባንዳ ነው ከቅሌት ነፃ ለመሆን አደብ የሚያስፈልገው።

እንደዚሁም አንዳንዶች ማወቅን አቅለው ያዩ ጥልቅ ግንዛቤ የሚያንሳቸው ታሪክን፣ ኅብረተሰባዊ ሳይንስን መሰረት ያላደረገ የኦሮሞ "ሕዝብ ዝሆን" ነው፣ "ሕዝብ ወደፊት ይወስናል" እያሉ ያልሆነ ታሪክና የተሳሳተ ቁጥርን ለማውራት የሚሞክሩትን ከአንዳንድ ጽሑፎቻቸው ለመረዳት ተችሏል። ለዚህ ሁሉ ከማመን ማወቅን ብታስቀድሙ መልካም ነው።

ያለፈውን ችግሮችና አዜዎችን ለመውቀስ አንተ ለመጪው ትውልድ መልካም ማድረግ ስትችል ነው። አንተ ግን እንኳን መልካም ነገር ለማድረግ ቀርቶ አደብ መግዛት እንኳን አልቻልክም።

በሀሰት የአንድነት ታሪክን ከመካድ፣ በውሸት ቁልቁለት ቅሌትን አንግቦ ከመንደርደር የኢትዮጵያ ሕዝብ ማንነቱን፣ ምንነቱን ምን እንደሚፈልግና ምን ማድረግ እንደሚሻ ጠንቅቆ መረዳት ያስፈልጋል። ምንጊዜም ለአንድነቱ፣ ለኢትዮጵያዊነቱ ለሰንደቅ ዓላማው ለክብሩ ይሞታል።

የኢትዮጵያን አንድነት አጠንክሮ ህልውናውን ለመጠበቅ፣ ሞራል፣ ክብርና ኩራቷን ለመመለስ ዛሬም እንደ ትናንቱ አንድነታችን ወሳኝ ኃይላችን ነው።

ኢትዮጵያዊያን ትውልድን በኢትዮጵያዊ ማንነቱና ሥነ-ምግባር፣ ኢትዮጵያዊ ወግና ባህል ለመቅረጽና ለማነጽ ዝግጁዎች በመሆን ሥርተን የምናሳየው የራሳችን አኩሪ ሥራ ሲኖረን እንጂ ሌላው የሰራውን ታላቅና መልካም ምግባር በማወደስ ወይንም በመኮነን የራሳችንን ባዶ አድርገን ባዳነትን ለመጪው ትውልድ እንዳናወርስ ልንሰጋና ልንጨነቅ ይገባል።

ኢትዮጵያ ስመ ጥሩ የሆነች ባለ ጥሩ ምግባር ታሪካዊት፣ ዛሬ የተፈጠረች ሳይሆን የረጅም ዘመን ታሪክ ባለቤት ጥንታዊት አገር ናት። ለኛ ለኢትዮጵያዊያን ብቻ ሳይሆን ዓለምን ያስደነቀ አርአያነት ያለው አኩሪ ታሪክ አስመዝግባለች። የሥልጣኔ ምንጭ፣ የነፃነት ምዕራፍ እንደሆነች በሰፋት ይተረካል። በመጽሐፍ ቅዱስ፣ በቅዱስ ቁርአንና በሌሎች የሃይማኖት መጻሐፍት ተደጋግማ የተጠቀሰች ስትሆን እንደዚሁም በፈላስፋዎችና በጸሐፊዎች በእነ ሆሜር፣ ጊቤንስና ሂሮዶተስ ስለ ኢትዮጵያ ታላቅነትና ስመ ጥሩነት በአክብሮት በሰፋት አትተዋል- ጽፈዋል።

ኢትዮጵያን በየዘመኑ የቅርብና የሩቅ የተመኛት፣ የከጀሏትና በሰበብ አስባቡ ጣልቃ እየገቡ ሰላምና እርጋታ የነሷት፣ እያፈራረቁ፣ እያከታተሉ ያጠቋት ቅኝ ገዢዎች፣ ወራሪዎችና ተስፋፊዎች ያደሟት አገር ብትሆንም በአንጻሩ ድልን ደጋግማ የተጎናጸፈች ናት። ጠላቶችዋን አብዛኛውን ጊዜ በዘዴ፣ በብልሃትና በትዕግሥት የቀረውን ደግሞ በኃይል መክታ አንድነቷን፣ የሕዝቧን ኅብረት በጀግንነት ጠብቃና አገራዊነቷን አስከብራ ታፍራ የቆየች የአኩሪ ታሪክ የጀግኖች አገር ናት።

ሕዝቧ አንድነቱን፣ ማንነቱን ተሳስሮና ተጋምዶ እንዲጠነክር ያስቻለውን፣ ለኢትዮጵያ አገራዊ ታላቅነት ከሁሉም የተለያዩ ቋንቋ ማኅበረሰብ እንዲሁም ከእያንዳንዱ ቤተሰብ ቢያንስ አንድ ሰው ሕይወቱን የተሰዋበት ወይንም አካሉን በመሰዋዕትነት የከፈለበት ድንቅዬ ታሪክ አለው። ይህች በአንድነታችን ክንድ በድላችን የተገነባች አገር የሁላችን መመኪያ፣ መኩሪያ ምንጊዜም ኢትዮጵያ ናት።

ከጥንት ከጧት ጀምሮ ያለውን የኢትዮጵያ አንድነት ለማስከበር እንደነ አፄ ቴዎድሮስና አፄ ዮሐንስ የመሳሰሉ ነገሥታት የሕይወት መስዋዕትነት ከፍልዋል። አፄ ምኒልክም የጣሊያን ወራሪ ጦር አደዋ ላይ ድል መተው የአገሪቱን አንድነት አስጠብቀዋል። አፄ ኃይለ ሥላሴ የአገሪቱን ሉዐላዊነት አንድነት በፅኑ መሰረት ላይ አጥብቀው ወደ ዘመናዊ ሥልጣኔ አሸጋግረዋል።

ኢትዮጵያ ነፃነት አፍቃሪ በመሆንዋ ለዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ የነፃነት አስተዋጽኦ አድርጋለች። በኮሪያ በኮንጐ ለተደረጉ ሰብዓዊ ትግሎች የሰው ሕይወት ሳይቀር አበርክታለች። በዚህና በሌሎችም ሰብዓዊ ተግባሮች ኢትዮጵያ በአገርነቷ፣ በታሪኳ፣ በሕዝቦቿ አንድነት፣ በአርአያ በአክብሮት በብዙ አገሮችና ሕዝቦች የምትታይና የምትደነቅ አገር ናት።

እምነትን፣ ትዕግስትንና ጽናትን ፈታኝ በሆነ ዘመን ላይ ነው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት የሚገኙት። ይህን በድል አድራጊነት ለመወጣትና አልፈን ለመጪው ትውልድ የተሻለ ዘመን ለማውረስ ራዕይ ካለን ማድረግ ያለብን፣ ኢትዮጵያዊ ቃል-ኪዳን ማጎልበትና ኢትዮጵያዊ ማንነትን ለአፍታ እንኳን መዘንጋት የሌለብንም መሆኑን ነው።

***ኢትዮጵያዊነት ያብባል!!***

***የተገንጣይና የአለቅላቂዎቻቸው ሴራ ይከስማል !!***